# እየበላ ለሚከሳ እየመከሩት ለሚረሳ ምን መድሀኒት አለው?

ዘነበ በቀለ

በዘመናችን ሁሉም ነገር የተገላቢጦሽ በመሆኑ እየበሉ ቢከሱ እየተመከሩ ቢረሱ "አጀብ!" ማለት ሞኝነት ነው። መብሉም ከሰውነት ምክሩም ከህሊና ዳኝነት አለመዋሃዱ የጊዜ ነውና!!

አሻቅበሽ ምቺው - ሰማዩን በእንቧይ
ተሽቆልቁሎ ሲወርድ - ሲፈርጥ እንዲታይ!

እንዲሉ! የወረወሩት እምቧይ በወዳጅ አናት ላይ እንዳይፈርጥ ማድረግ የማንኛውም ወርዋሪ የሞራል ግዴታ ነው። ወያኔን መኮነን ማውገዝ ካፍ በላይ የሚውልበት ዘመን እንዳይርቅ የወርዋሪዎችን ጠንቃቃነት ይጠይቃል።

የተደራጀ ሀይል ማንኛውንም ጭቆና ሊያስወግድ የሚችል መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ነገር ግን ወያኔም ሆነ ተባባሪዎቹ ከፍተኛ ትግል የሚያደርጉት የኢትዮጵያ ህዝብ በሀገራዊና በህዝባዊ ስሜቱ እንዳይደራጅ ለማድረግ ነው። በጎጥና በሰፈር የሚደራጀው ሀይል ለታላቁ ሀገራዊ ስራ ብቃት እንደማይኖረው ስለሚያውቁት አሰላለፉን በዚያ በኩል ቢያደርግ ጭንቀት የላቸውም ወያኔዎች። በመሆኑም ተባባሪዎቻቸው መደራጀት በቋንቋ ደረጃ እንዲወርድ አዋጥተዋል። ትግል በግል ጥቅም ላይ እንዲውል አድርገዋል። የእነ አቶ ቡልቻ ደመቅሳና፣ የእነ አቶ ገብሩ አስራት ፡አረና፡ ፓርቲ አይነቶቹ ለወያኔ የክልል ፖሊሲ የሚታገሉ መሆናቸው ሀቅ ነው። እንዲህ አይነቱ ድርጅትም ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት የሚጠቅም ሳይሆን ለወያኔ የፓርላማ ቡና መጠጫ ወሬ የሚረዳ መሆኑ ጥርጥር የለውም። እነዚህን መሰል ክፍሎች አብዛኞቹ ዲሞክራሲን በገደብ ለመቀበል ነው ፍላጎታቸው እንጂ! ከነ አቶ መለስ ፓርቲ በይዘት አይለዩም። ኢህአፓን ከነዚህ ሁሉ ስብስቦች የሚለየው ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊነቱ ነው። ላልተሸራረፈ ህዝባዊ ዲሞክራሲ ተግባራዊነት መታገሉ ነው። ለዚህም ተግባራዊነት መስዋዕት ለመክፈል ቆርጠው የተነሱ አባላት ያሉት መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያለምንም ገደብ በዓላማና በግለሰብ መብት ላይ ያተኮረ አደረጃጀት መፍትሄ ሊሰጠው እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቀዋል።

ይህ ሲባል በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ የተደራጀ ሀይል በጓደኝነት፤ በቋንቋ፤ በሰፈርልጅነት ወዘተ. የተዋቀረ ማህበር መፍጠር ማለት አይደለም። ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በጎ ራዕይ ያለው ለመብቱ ሊቆም የሚችል ጠንካራና ቆራጥ አመራር የሚሰጥ ድርጅት ማለት በመሆኑ ኢህአፓን በልምድና ተመክሮ የሚመጥነው አይኖርም። ይህ ጥያቄ ደግሞ

ለኢ.ህአፓ ዛሬ የተነሳ ሳይሆን፤ ከተማሪነት እስከመምህርነት፤ ከወጣትነት እስከ ሽምግልና ዘመን ባስቆጠረ ልምድ የተገነባ ትግል ነው፤ አባትና ልጅን፤ ልጅና የልጅልጅን ያፈራ ትግል ነው። ትግል አበቃ አቆመ! የሚሰኝለት  አይደለም። ማብቂያው የኢትዮጵያ ህዝብ መብት መረጋገጥ ብቻ ነው። እንደ ኢ.ህአፓ አይነቶቹ ህዝባዊ ድርጅቶች መተክላቸውን ከህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ጋር አቆራኝተው ሲጓዙ "ትግሉ ነው ህይወቴ" እያሉ በመዘመር ነው። አህአፓ ህዝባዊ የሆነ መንግስትን ለመፍጠር ሲያደራጅ፡ ስለ መሬት ላራሹ ሲጮህ፤ ስለ ቋንቋ ስለ ባህል ዕኩልነት ሲሰብክ፤ ከጎጥ ስብስቦች መንጋጋ ውስጥ ህዝብ እንዳይገባ እያስጠነቀቀ ነው። ሲያታግል ሲታገል በርካታ መስዋዕትነትን የከፈለው፤ የሀገሪቱና የህዝቧ ዕጣ ክፍል መለያየት እንዳይሆን ነው። ወሬኛውን፤ አስመሳዩን፤ ጥቅመኛውን፡ ሀገር ሻጩን፤ ኢ.ህአፓ የታገለው፤ "ሀገርና ህዝብን የምትሹ! ታገሉለት አትሽሹ" እያለ በመዘመርና በማዘመር ነው። እነዚያ መስዋዕት የተከፈለባቸው ህዝባዊ ጥያቄዎች እስካሁንም ድረስ መልስ ያላገኙ በመሆናቸው፤ መዝሙሩም ትግሉም መቀጠሉ ግዴታ ነው። መንግስት የህዝብ አልሆነም። መሬት ላራሹ አልዋለም። የግለሰብ ዲሞክራሲያዊ መብት አልተጠበቀም። ጭርሱኑ ህዝቡ የሚቀምሰው በማጣት ላይ ነው። ወዘተ.

ታዲያ በምኑ ላይ ነው ኢ.ህአፓ ትግሉን እንዲያቆም የሚገፋፋው? በምን ጉዳይ ላይ ነው እርብርቦሹ? ለማን ጥቅም ሲባልስ ነው በአሁኑ ሰዓት ግምባር ቀደም ተወቃሽ ኢ.ህአፓን ማድረግ የሚፈለገው? ወያኔን ጥላ ከለላ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ክፍሎች ጥቅማቸውን ለማስከበር በሚያደርጉት ረብረብ፤ ኢ.ህአፓ ህዝባዊ ጥያቄውን ሊሰበው አይገባም። የወያኔ ትልቁ የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሆነው ጎሳዊ ባህል እንኳ በወጉ ህልውናውን ጠብቆ የሚጓዝ አይደለም። እንዲያውም በብዙ መልኩ ድሮ ከነበረው በበለጠ አደጋ ላይ ነው የሚገኘው። ዛሬ በአውሮጳውያንና በሩቅ ምስራቅ ባህሎች እየተበረዘ ያለበት ሁኔታ ላይ ስለሆነ፤ የኦሮሞም ሆነ የጉራጌ፤ የወላይታም ሆነ የአማራ ባህሎች እየጠፉ ለመሆናቸው ብዙ መረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ሌላው ቢቀር በሴንቲሳይዘር እየተደገፈ የሚቀርበው የባህል ዘፈን ኢትዮጵያዊ ባህልን እየሸረሸረው ነው። ይህ አይነቱ ስራ በወያኔ ስልጣኔና፤ እድገት፤ ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ለኢትዮጵያውያን ግን የባህል ብረዛና ወረራ ከመሆን አያልፍም። ደርግ የህዝቡን ባህላዊ ዕሴቶች ሲያጠፋ፤ ሲለውጥና ሲበርዝ በአብዛኛው በድንቁርናው የፈፀማቸው ነበሩ። ለወያኔ ግን ሆን ተብሎ በህዝብ ውስጥ የሚገፋ ሀሳብ ነው። ወያኔ በዕድገት አሳቦ ሀገሪቱንም ሆነ የህዝቡን ባህላዊ ቅርስ እያጠፋ መሆኑ ግልፅ ነው።

ስለዚህም ኢ.ህአፓን መወንጀሉ የህዝብ ጠላትነት እንጂ በወዳጅነት ሊያስፈርጅ የሚያስችል ሀቅ የለውም። ምክንያቱም ትግሉ ገና በርካታ

EthioLion.com

ቆራጥ ታጋዮችን የሚፈልግ መሆኑ እየታወቀ። ህዝብ የተነሳለትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉ እንደ ኢህአፓ ያሉ ፓርቲዎችን መቃወም ወያኔን ከመደገፍ ተለይቶ ሊታይ አይችልም። ስለዚህም ህዝባዊ ወገናዊነትን የያዙ ድርጅቶች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ናቸው። ኢህአፓ ደግሞ ገና ከጅምሩ የፓሪ ሞድ ቀሚስ ፋሽን ሾው ተብሎ፣ በዚያም ሳቢያ የሌሎች ባህላዊ ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እንዳያርፍ ሲታገል ከነበረው ተራማጅ የተማሪዎች ማህበር ማህፀን የተገኘ በመሆኑ ህዝባዊ ክዳት አይነካካውም። ኢህአፓ!

ህዝብና ሀገርን የምትሹ!
ታገሉለት አትሸሹ!

እያለ የታገለ ያታገለ እስካሁንም ከትግሉ ሜዳ ያልወጣ ድርጅት ነውና ሊከበር ይገባዋል። በመሆኑም ለህዝባዊነቱና ለሀገር ፍቅሩ ኢህአፓን መጠራጠር እራስን ካለማመን የሚመነጭ መሆን ነው የሚችለው። ከህዝባቸው ተቆራኝተው ችግሩን ተጋርተው መከራውንም አብረው የከፈሉ አያሌ የኢህአፓ ታጋዮች መኖራቸው የሚያስደስት እንጂ የሚያሳዝን ሊሆን አይችልም። እነ ፀጋዬ ደብተራውንና ጋይምን የመሳሰሉ ቆራጥ ታጋዮችን ያፈራ ድርጅት በመሆኑ የዓላማ ፅናቱ አጠራጣሪ አይደለም። ታዲያ! አንዳንድ ነቃፊዎቹ ኢህአፓ ስህተት ፈፅሟል ሲሉ፣ ነጥባቸውን በውል ለማስቀመጥ ይቸገራሉ። ህዝባዊ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳቱ ነው ኢህአፓ የሚወነጀለው? ወይስ በትግል መስዋዕትነት በመክፈሉ? ወይስ ጓዳ ጎድጓዳውን ለቱሪስቶች ሁሉ ባለማስጎብኘቱ? የቱ ላይ ነው ስህተት ተብሎ የሚጠቀሰው? ይህ ዛሬ ባሳዛኝ መልኩ የሚስተዋለው የሀገር አንድነት አደጋ ላይ የመውደቅ ሁኔታ የተከሰተው የነመንግስቱ ሀይለማርያም ኢሰፓ ለህዝባዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ባለመቻሉ እንጂ! ኢህአፓ ጥያቄዎቹን በማንሳቱና በመታገሉ ምክንያት የተፈጠረ አይደለም።

ይህን የዛሬውን የወያኔን የአፓርታይድ መንግስት የፈጠረው የኢህአፓ ትግል የሚመስላቸው ሁሉ፣ መለስ ብለው እራሳቸውን ሊመረምሩ ይገባል። ምክንያቱም ኢህአፓ አንስቷቸው የነበሩትና የሚታገልላቸው አላማዎች ህዝባዊ መንግስት! መሬት ላራሹ! የዲሞክራሲ መብት ያለገደብ! ወዘተ. ሁሉም እስከዛሬ ያልተፈቱ ጥያቄዎች ናቸውና። እነዚህን ጥያቄዎች እየሸራረፉ ለመተርጎም የተሞከረበት የበራገሮች ትግል፣ ደግሞ ደጋግሞ ስለፎረሸ፣ ታጋዮቹም የውጭ ተመልካች እስከመሆን የደረሱበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው። በመሆኑም ኢህአፓ ትግሉን ትቶ ሊቀመጥ የሚያስችለው ታሪካዊ ሀቅ የለም። ጥያቄዎቹ ከዚህ በፊት የነበሩትን መንግስታት ሲያስጨንቁ እንደኖሩት ሁሉ ወያኔንም ወጥረው የሚይዙት ህዝባዊ ጥያቄዎች ናቸው። በክልል መንግስታት ምስረታ ሰበብ ህዝባዊ የሆነውን የዲሞክራሲ ጥያቄ ሊያድበሰብሰው ወያኔ! በፍፁም አይቻለውም።

EthioLion.com

ኢ.ህአፓ በወያኔ ላይ እጁን ሰብስቦ የተቀመጠ አለመሆኑን ከወያኔ በላይ የሚያውቀው ላይኖር ይችላል። አንዴ ድርጅቱ ጠፍቷል። ሌላ ጊዜ ጥቂት ሰዎች የተሰባሰቡበት ነው እያለ ሲቀላምድ የነበረው ወያኔ፤ ዛሬ ይህንንም ያንንም ላለማለት ተገዷል። ኢ.ህአፓ ማን እንደሆነ በውል እየተገነዘበው ያለበት ወቅት ላይ ነውና!

አንዳንድ ተስፈኞች ወያኔን ለምነን ለማደር አላስቻለንም ብለው ኢ.ህአፓን ሊከሱት፤ ሊኮንኑት ቢሞክሩም ወያኔን የመርዳት ሀይላቸው ባዶ መሆኑን ይገነዘቡታል። ወያኔ የታሰረበትን ገመድ ሲስብ እራሱን በራሱ ተብትቦ ለመውደቅ የሚወዛዋዝ በመሆኑ ከመንከባለል እንደማይድን ያውቀዋል። ተስፈኞቹን አሰማርቶ በስም ማጥፋት ዘመቻ በኢ.ህአፓ ላይ እንዲሰለፉ ያድርግ እንጂ! ወያኔ የታሰረበትን ገመድ ውል የሚያውቀው ኢ.ህአፓ እንደሆነ አይስተውም። ሀገር ወዳዱ በሚደሰኮርለት ፕሮፓጋንዳ ሳይዋዛ፤ በወሬ ሳይሆን በተግባር አይቶ፤ ሀቁን መርምሮ መፍረድ ብልህነት ነው የሚሆነው። አለበለዚያ ያረጀ ያፈጀ ፀረ ኢ.ህአፓ ዘመቻ ፊትም አልጠቀመ፤ አሁንም አይጠቅምም። በየጊዜው የወያኔን አጀንዳ እየያዙ በመምጣት ሊያደናግሩ የሚጥሩ ሁሉ በራሳቸው ዕድሜአቸውን ሲያሳጥሩ ታይተዋል። በፊተኛው ዘመን ኢ.ህአፓ የትግል ስህተት አድርጓል ብለው ለሚኮንኑ ወገኖች፤ ነጥባቸው መሆን የሚችለው፤ አንደኛ ህዝባዊ ጥያቄዎቹን ኢ.ህአፓ ማንሳት አይኖርበትም። ሁለተኛም እስካፍንጫው የታጠቀ መንግስት ጋር ለነዚህ ህዝባዊ ጥያቄዎች ተብሎ ትግል መግጠም አያስፈልግም ብሎ መደምደሚያ ላይ መድረስ ነው።

ይኸ ደግሞ ተቀባይነት የሚኖረው ጉዳይ አይደለም። ሁለቱም አመለካከቶቻቸው ስህተት ውስጥ የሚከቱ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም። ትግል አላማን ጨብጦ፣ ሀይልን እያካበቱ ጉልበትን እያጠነከሩ በቆራጥነት መጓዝን የሚጠይቅ እንጂ! አቅም እስካበጅ ድረስ ማንም ይግዛኝ ብሎ መወሰንን አቢ.ይ ተግባሩ አያደርግም። በመሆኑም ኢ.ህአፓ በታሪኩ ውስጥ የተንበርካኪነት ስሜት አልነበረውም ወደፊትም አይኖረው። የትግል ታሪኩ የሚመሰክረው ያንን ነው። የኢ.ትዮጵያ ህዝብ  ጥያቄ መልስ ባላገኘበት ሁኔታ፤ በፈለገው መጠን ወያኔ በባዕዳን እየታገዘ ቢንቀሳቀስም፤ ኢ.ህአፓ ወጥሮ እንደሚታገለው ጥርጥር የለውም። ይህ የጀግኖች ስብስብ በወዳጆቹ ይበረታታል እንጂ! የፈሪነት ካባ እንዲደርብ አይደረግም። ቆራጥና በሳል አባላትን ያፈራ ድርጅት ነውና ለሰርጎ ገቦች ባይመች ሊቀየሙት አይገባም።  ዳሩ ግን! እየበላ ለሚከሳ እየመከሩት ለሚረሳ ምን መድሃኒት ሊገኝ?

ቸር ይግጠመን!!

EthioLion.Com